# ተቃዋሚዎች የዴሞክራሲ ሒደቱ አጋር ናቸውን?

**ከሃብሮማይ** 07/22/09
ghabrom@yahoo.com

የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ መሰረት ለመጣል ሆነ ለማጎልበት የሚቻለው የተለያዩ ተቋሞችን በማጠናከር መሆኑ እሙን ነው፡፡ለዚህም ነው የበለፀጉት አገሮች ዴሞክራሲያቸው የተሻለ ሆኖ የምናየው፡፡

የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ገንብተዋል የምንላቸው ሃገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ዴሞክራሲ የብዙ አስርት አመታት ዘገምተኛ የጉዞ ውጤት መሆኑ ካለፈው ታሪካቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ዴሞክራሲያቸው አሁን ያለበትን ደረጃ እንዲደርስ የዴሞክራሲ ተቋሞቻቸውን ትልቅ አስተዋፆ ማድረጋቸውንም በተጨባጭ እያየን ነው፡፡እነዚህን ተቋማት ባይጠነክሩ ኖሮ አሁን ያሉበትን ደረጃ ባልደረሱ ነበር፡፡

ከነዚህ የዴሞክራሲ ተቋማት መካከል የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዱና ዋነኛዎቹ ናቸው፡፡በነዚህ የበለፀጉ አገሮች የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያየ ግልፅ የሆነ አቋም ይዘው ምክንያታዊ በሆነ መንገድ አገራቸው ያስፈልጋታል ብለው ያመኑለትን አቅጣጫ ለሕብረተሰቡ በሚገባ አስታውቀው ህዝቡም ተጨባጭ የሆነ መረጃ ይዞ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የትኛውን ፓርቲ እንደሚጠቅመው በማጤን በሰጡት መረጃ ላይ ተሞርኩዞ የፈለገውን ፓርቲ ይመርጣል፡፡

ወደ አገራችን ስንመጣ የዴሞክራሲ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት በዴሞክራሲያዊ አኳሃን እንዲሰራና እንዲደራጅ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡እያደረገም ይገኛል፡፡

ሶስቱ አካላት ህግ አውጭው፤ህግ አስፈፃሚውና ህግ ተርጓሚው በስርዓቱ ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና ለይቶ ሚናቸውንም በአግባቡ እንዲጫወቱ ለማድረግ

የሚያስችል ስራ ተጠናክሮ እየቀጠለ መሆኑ ዴሞክራሲያችን በበለጠ ጥልቀት እንዲኖረው በየጊዜው በመውጣት ላይ ያሉ ህጎች በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ይሁንና ዴሞክራሲ በመንግስት ተቋማት ብቻ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ስላልሆነ በተለይ የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ ማረጋገጥ እንደ አንድ መሰረታዊ መርህ ተደርጎ በተወሰደበት በኛ አገር የህዝብ ማህበራትንና ተቋማት ተገቢ ድርሻቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡

በዚህ ረገድ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች ፤የመገናኛ ብዙሃን፤የሙያና የብዙሃን ማህበራት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ስለሆነም የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዓላማን ለማሳካት ፤ተቋማዊ መሰረቱ ለማስፋፋትና የጋራ ዴሞክራሲያዊ አመለካከትና እምነት ለመፍጠር የተጠቀሱትን ድርጅቶችና ተቋማት መመስረት፤ ማጠናከርና ተልኳቸውን በብቃት እንዲፈፅሙ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

በ 1983 ዓ.ም በደርግ መንግስት ውድቀት ማግስት ከነበረው ሁኔታ ተነስተው አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ኢትዮጵያ ከቀድሞዋ ዩጎዝላቭያ እጅግ የባሰ ደም መፋሰስና ጠቅላላ መበታተን ይከሰትባታል ብለው ተንብየው ነበር፡፡አገራችን በዜጎችና ህዝቦች መብት መታፈን በተፈጠረውና በተበባሰው ቅራኔ ምክንያት በአስከፊ ጦርነት ውስጥ ተዘፍቃ ክፉኛ የማሰነችበት ሁኔታ ውስጥ በነበረችበት ወቅት የቀረበ ትንበያ ስለነበር ይህን ያህል መስመር የለቀቀ ትንበያ ነበር ማለት አይቻልም፡፡ይሁን እንጂ መንግስት የህዝቡ ጥያቄ በማዳመጥ አፋጣኝ የሆነ እርምጃ በመውሰዱ አገራችን የዓለም ተንታኞች እንደተነበዩት ሳይሆን በአንፃሩ ህዝቦች በፍላጎት፤በመፈቃቀርና በመከባበር የሚኖርባት ኢትዮጵያን እውን ሆናለች፡፡ስለሆነም አሁን በአገራችን የዴሞክራሲ ተቋማት ከነበረበት ከዜሮ ተነስቶ እስከ ታችኛው የእርከን ደረጃ የተለያዩ ነፃ ማህበራት ማለትም የወጣት፣የሴቶች፣የአርሶ አደር...ተቋቁመው ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ድርሻቸውን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡

የአገራችን ዴሞክራሲ ሊዳብር የሚችለው ተቋማትን በማጠናከር ስለሆነ አሁን በተጨባጭ የተለያዩ የብዙሃንና የሙያ ማህበራት በብዛት እንዲመሠረቱና አባሎቻቸውን እንዲያደራጁ እየተደረገ ነው፡፡የተለያዩ ማህበሮች በተናጠል ችግሮቻቸው በቀላሉ ሊፈቱ ስለማይችሉ አንድ ዓይነት ዓላማ ያላቸው ማህበራት ተደራጅተው ፌዴሬሽን እንዲመሰርቱ ከዚያም አልፈው ኮንፌዴሬሽን እንዲመሰርቱ ከዚያ አልፈውም የዓለም አቀፍ ኮንፌደሬሽኖች አባል የሚሆኑበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡እነዚህ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ማህበራት ለዴሞክራሲ ግንባታው ትልቅ አስተዋፆ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ በቅርቡም የሴቶች ፌዴሬሽን ና የወጣቶች ፌዴሬሽን መመስረቱ ለዴሞክራሲ ስርዓቱ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡መንግስትም ከነዚህ ማህበራት የሚነሳውን ጥያቄ እያዳመጠ ጥያቄያቸውን በየደረጃው እየፈታ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ ከጀማሪነቷ አኳያ ሲታይ በጣም ብዙ የዴሞክራሲ ተቋማት ገንብታለች፡፡ፓርላማው ዋነኛው የዴሞክራሲ መገለጫ ነው፡፡በፓርላማው የተለያዩ ክርክሮች ይካሄዳሉ ለህዝቡም በሚድያ እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡የመንግስትና ብዛት ያላቸው የግል ሚድያዎች አሉ፡፡ነፃ ፍርድ ቤት ና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ ተቋቁሟል፡፡ይህ ደግሞ የአገራችን ዴሞክራሲ መሰረቱ ተቋማት (democratic institutions) መሆናቸውን በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላም በሕገ መንግስቱ ላይ ከአንቀፅ 14 ጀምሮ እስከ አንቀፅ 28 የሚናገረው ስለ ሰብአዊ መብቶች ነው፡፡ሕገ መንግስቱ ለሰብአዊ መብት ትልቅ ትኩረት ሰጥተዋል፡፡እነዚህን መሰረታዊ መብቶች የዜጎች ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ ፣የማይጣሱና የማይገፈፉ መሆናቸው በሕገ መንግስቱ በማያሻማ መልኩ ተቀምጠዋል፡፡

እነዚህን መሰረታዊ መብቶች በአግባቡ ተግባር ላይ እንዲውሉ የሰብአዊ መብት ኮሚሽንና የእምባ ጠባቂ ተቋም መቋቋም እንዳለባቸው ሕገመንግስቱ አስቀምጧል፡፡

የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋና ዓላማ ስለ ሰብአዊ መብት በሕብረተሰቡ ላይ ግንዛቤ መፍጠርና የሰብአዊ መብት ጥሰት ባለበት አስፈላጊ የሆነ እርምጃ መውሰድ ነው፡፡ይህ ኮሚሽን በሰብአዊ መብት ጥሰት ዙርያ የደረሰበትን ጥቆማ ሁሉ የመመርመር ሙሉ ስልጣን አለው፡፡

የእምባ ጠባቂ ተቋምም ዋና ዓላማው መልካም አስተዳደርን ማስፈንና አስፈጻሚውን አካል በሕግ የተቀመጡትን የዜጎች መብትና ጥቅም በተግባር ላይ እያዋለ መሆኑና አለመሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

እነዚህን ሁለት ተቋሞች በሰብአዊ መብት ዙርያ የማይተካካ ሚና አላቸው፡፡ኮሚሽኑ በሰብአዊ መብትና ነጻነቶች ዙርያ ነው ፤ የእምባ ጠባቂ ተቋም ደግሞ በአስተዳደር ዙርያ ያሉ ግድፈቶች ነው የሚሰራው፡፡ሁለቱም ተጠያቂነታቸው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡እነዚህ ተቋሞች በሰብአዊ መብት አያያዝ ዙርያ አበረታታች የሆነ ስራ በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሂደትም አጋርነታቸውን አበረታታች በሆነ መልኩ እያከናወኑ ናቸው፡፡ከዚህ በበለጠ መልኩ መስራት እንዳለባቸው ግን እሙን ነው፡፡

በሌላ ፓርቲዎች ለቆሙለት ዓላማና የህብረተሰብ ክፍል በዴሞክራሲያዊ አኳሃን በመታገል ከሚያበረክቱት አስተዋፆ ባሻገር አላማቸውን ማራመድ የሚችሉት የዴሞክራሲ ስርዓት ሲገነባ መሆኑን በመገንዘብ የዴሞክራሲ ባህል እንዲያበብ፤የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ መጫወት እንዳለባቸው አያጠያይቅም፡፡ይሁን እንጂ የአገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተቋማትን እንዲጠናከሩ ማድረግን እንተወውና እንዲፈጠሩም ፍላጎት ያላቸው አይመስልም፡፡ለምሳሌ ያህል የወጣቶች ፌዴሬሽን ሲቋቋም እሰየው ብለው መቀበል ሲገባቸውና የወጣቱን ጥያቄ ለመመለስ ጥረት ከማድረግ ይልቅ ፌዴሬሽኑ ከማንም የፖለቲካ ጫና ነፃ ሆኖ ሳለና ወጣቱ ፍላጎቱን ደረጃ በደረጃ ለሚሟላትና የህብረት ድርድሩን (collective bargaining) ለማጠናከር ያቋቋመው ተቋም ሆኖ ሳለ ፌዴሬሽኑ የገዢው ፓርቲ መሳርያ እንደሆነ አድርገው

መግለፃቸው ስሰማ እነዚህ ፓርቲዎች የተለያዩ ተቋማት ሲፈጠሩ ማበረታታት ሲገባቸው ገና ከመጀመርያው ለማዳከም ማሰባቸው የነዚህ ፓርቲዎች የነገ ራእይ ምን እንደሆነ ግራ ነው የሚያጋባኝ፡፡ስለዚህ በአገራችን ያሉ የተለያዩ ፌዴሬሽኖች በመፈጠራቸው ደስተኞች አይደሉም ወደ ሚል ድምዳሜ የሚያስኬድ ይመስለኛል፡፡ይህ ደግሞ በተቋሞች ያላቸውን አመለካከት አናሳ መሆኑ ነው የሚያሳየው፡፡በተቋም ላይ ያልተገነባ ዴሞክራሲ ደግሞ ምን ዓይነት ዴሞክራሲ እንደሚሆን እኔ እንጃ፡፡

በተጨማሪ ፓርቲዎች ዴሞክራሲያዊ የሆነ ባህሪይ ሊኖራቸው ይገባል፡፡እነዚሁ ፓርቲዎች አንድ የፖለቲካ ዓላማን ለማራመድ፤በዚህ የፖለቲካ ዓላማ ለመሰባሰብ የሚፈልጉ ዜጎችን በሙሉ ለማሰባሰብ የሚጥሩና መነሻ መድረሻቸው ዓላማቸው ሊሆን ይገባል፡፡ዓላማቻቸውን ለማራመድ ዓላማቸውን ራሱ ጠንቅቆ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ከዚህም ባሻገር ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አማራጮችን በመተንተንና በማቀናበር ለህዝብ የማቅረብ ዓቅም ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ የአገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመርሁ በዘለለ መልኩ ለህዝብም ለአገርም የማይጠቅምና ምክንያታዊ ያልሆነ ትችት ሲሰነዝሩ ፤ግልፅ የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም አለመያዝ፣ ሽንፈትን በፀጋ አለመቀበል፣ የመቻቻል አቅም ዜሮ መሆን፣ አደገኛ የፕሮፓጋንዳና የኮሚዩኒኬሽን ስልት፣ ሂስና ነቀፌታ ለመቀበል ዝግጁ አለመሆን፣ ልዩነትን ወደ ጥላቻ መቀየር፣ አባልን በዓላማ ከማሰባሰብ ይልቅ በስሜትና ባልሆነ መረጃ ማቅረብና ማራቅ፣ በገንዘብ ዙሪያ ምግባረ ብልሹነት፣ እርስ በርስ መወነጃጀል ወዘተ… መለያቸው ሆነዋል፡፡እንደዚህ ዓይነቱን የፖለቲካ አመራር ለመስጠት የማይችል ፓርቲ አንድም የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም ፤አለበለዚያም ተልእኮውን በአግባቡ ሊወጣ የሚችል ፓርቲ አይደለም፡፡ስለሆነም በኢትዮጵያ ያለውን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት ላይ ተቃዋሚዎች አጋር ናቸው ለማለት የሚያስችል በቂ ምክንያት የለኝም፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ዴሞክራሲያችን ጥልቀት እንዲኖረው የፖለቲካ ፓርቲዎች  ጠንክረው መስራት እንዳለባቸው እሙን ነው፡፡ የኛ አገር የፖለቲካ ተቃዋሚዎች የአገራችን ፖለቲካዊ፤ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከስሜት በዘለለ መልኩ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ነቅሰው በማውጣት ሕዝባችንን የሚጠቅም አማራጭ ይዞ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ፖሊሲያቸውና ስትራተጂያቸውንም ለሕዝብ በሚገባ በማቅረብ የሚመርጣቸውም ሆነ የማይመርጣቸው በመረጃ ተሞርኩዞ መሆኑን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ይሁን እንጂ ተቃዋሚዎች አገራችን እንዴት ከድህነት እናላቅቃት ምን ዓይነት ፖሊሲና ስትራተጂ ተከትለን ነው  ካለችበት ደረጃ በላይ ልናሳድጋት የምንችለው ብለው ተጨባጭ ፖሊሲና ስትራተጂ በመቅረፅ ፍልስፍናቸውን ማሳየት ተስኑዋቸዋል፡፡እነዚህ ፓርቲዎች ከተቋም ይልቅ ግለሰብ ፤ ከህግ ይልቅ ትእዛዝ ፤ ከምክንያት ይልቅ ስሜት ፤ ከመረጃ ይልቅ አሉባልታ ጎልቶ በሚታይበት ልማዳዊ አሰራር ውስጥ እየተሽከረከሩ ያሉ ናቸው ካልኩ የተሳሳትኩ አይመስለኝም፡፡

አሁን በተጨባጭ ይዘውት ያሉት አካሄድ ስገመግም ዴሞክራሲያዊ የሆነ አካሄድ አላቸው ብዬ አላምንም፡፡ምክንያቱም በሌሎች የበለፀጉ አገሮች እንደምናየው ታማኝ ተቃዋሚ (loyal opposition) በሚል ስያሜ የሚታወቁ የራሳቸው የተለየ ፖሊሲ ከማቅረብ ባሻገር ሕገ መንስትን የሚንድ ሃሳብና ተግባር የሚቃወሙ ናቸው፡፡ይህ የሚሆነው ፓርቲዎቹ የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት ሲኖራቸው ነው፡፡እንደዚህ ዓይነት አመለካከት በፓርቲዎች ሲኖር ደግሞ በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ መጫወት የሚገባቸውን የላቀ ገምቢ ሚና እንዲጫወቱ ያደርጋቸዋል፡፡የአገራቸው የዴሞክራሲ ሂደትም አጋር መሆናቸው አያጠያይቅም፡፡ የአገራችን ተቃዋሚዎች ግን ሕገመንግስቱ ከተመቻቸው የሚቀበሉት ካልተመቻቸው ደግሞ የሚሽሩት፤ህጋዊና ሕገወጥን እያጣቀሱ ሲጓዙ ነው የሚስተዋሉት፡፡ስለሆነም በአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ላይ እነዚህን ተቃዋሚዎች አጋርነት አላቸው ብየ ለማመን ያስቸግረኛል፡፡

በአገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ሊቀለበስ ወደማይችልበት ደረጃ ቢደርስም ይበልጥ ጥልቀት እንዲኖረው የተለያዩ ህጎችን ማውጣት እንደሚያስፈልግ እሙን ነው፡፡እነዚህን ህጎች ሲወጡ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ጊዜ ተወስዶ ምክክር ተደርጎበት በተወካዮች ምክር ቤት ፀድቀው ነው፡፡አንድ ነገር ህግ ሆኖ ከወጣ በዛው ህግ (existing law) ብቻ መጫወት እየተገባ የአገራችን ተቃዋሚዎች ግን እንደገና ተማምነው ባወጡት ህግ ሲከራከሩ ይታያሉ፡፡ይህ ደግሞ ነገሮችን ባለው ህግ መሰረት ዴሞክራሲያዊ ሆነው እንዳይሄዱ ጥረት እያደረጉ ያሉ መሆናቸው ነው የሚያሳየው፡፡እንደዚህ ዓይነት አካሄድ በማንኛውም መስፈርት በየትኛውን ዴሞክራሲያዊ አገር ፀረ ዴሞክራሲ ነው፡፡ስለሆነም የአገራችን ተቃዋሚዎች በአገራችን እያደገ ያለውን የዴሞክራሲ ሂደት አጋርነት አላቸው ብየ ለማመን ያቅተኛል፡፡

መንግስት በአገራችን ልማት፤ ሰላምና ዴሞክራሲ የማይነጣጠሉ፣ አንድ መሆናቸውንና የህልውና ጥያቄ መሆናቸውን ተገንዝቦ እነዚህን ለማሳካት የአቅም ግንባታ ስራን እንደ ቁልፍ ስራ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

ተቃዋሚዎችም ለዴሞክራሲ ግንባታ ወሳኝ ሚና እንዳላቸው በመገንዘብ በዴሞክራሲ ከዳበሩት አገራት ምሁራንን በማስመጣት ጭምር አቅማቸውን እየገነባ ይገኛል፡፡ በምርጫ ቦርድ በኩል የተደረገውን ስልጠና አስታውሳለሁ፡፡ ይህ መልካም ጅምር ተጠናክሮ መቀጠል አለበት እላለሁ፡፡

ይሁንና በአገራችን ያሉ ተቃዋሚዎች በመጀመሪያ መቅረፍ ያለባቸው የብዙ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት የጠየቀና በመጨረሻም በህዝብ ተሳትፎ እውን የሆነ ሕገ መንግስታችን ላይ ያላቸውን አመለካከት መቀየር ይኖርባቸዋል፡፡ይህ ሲሆን ነው በአገራችን ላለው የዴሞክራሲ ሂደት አጋር መሆን የሚችሉት፡፡ በዚህ ላይ የአቅም ግንባታው ሲጨመርበት የዴሞክራሲ ግምባታችን ካለው በላይ ሊጎለብት ይችላል፡፡

በመጨረሻ የአገራችን የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ህገ መንግስቱን በማያሻማ መልኩ በመቀበል ፣ ግልፅ የሆነ አማራጭ ፖሊሲ በማቅረብ ፣ ተቋሞችን በማበረታታት ፣ ባለውን ሕግ በመጫወት የአገራችንን የዴሞክራሲ ሂደት አጋር እንዲሆኑ እመኝላቸዋለሁ፡፡ሰላም!